# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

## ኢሕአፓ የኢራንን ሕዝብ ትግል ይደግፋል!!

ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ.ም.

ከጥቂት ቀናት ጀምሮ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ኢራናዊያን በተከታታይ “ድምጻችንን መልሱልን”፤ “አዲስ ምርጫ ይደረግ”፤ “ምንም ዓይነት መልክ ይኑረው አምባገነንነትን አንፈልግም”፤… በሚሉ መሪ መፈክሮች ዙሪያ ድምጻቸውን ሲያሰሙ ሰንብተዋል። የምርጫ ድምጽ በመሰረቅና የአክራሪ እስልምና አስተዳደርን በማስቀጠል በተለይም በወንድ ማናህሎኝነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የሚያምኑትን፣ የአህመዲኒጃድን አገዛዝ በመቃወም ተማሪዎች፥ አስተማሪዎች፥ የቢሮ ሠራተኞች፥ ወጣትና አዛውንት ሴቶች፥ በተለያዩ የሙያ መስኮች በሕዝቡ ዘንድ አክብሮትን ያተረፉ ታዋቂ ግለሰቦችና የመንግሥት ሠራተኞች ተካፋይ የሆኑበት የሀገራቸውን ሰንደቅ ዓላማ በማውለብለብ፤ አረንጓዴ ጨርቅ በክንዳቸው፣ በጭንቅላታቸውና በእጆቻቸው ላይ በማሰር የድል አርማ ምልክትን በጣቶቻቸው እያሳዩ ሕዝባዊ አመጽ እያደረጉ መሆናቸው በተለያዩ የዜና አውታሮች እየተስተጋባ ይገኛል።

በርካታ የፖለቲካ ታዛቢዎች እየገለጹ እንዳሉት ባለፉት በርካታ አመታት የምርጫ ደምጽ በአገዛዙ መስረቅ አዲስ ነገር ባይሆንም የዘንድሮው ግን የሕዝቡን ንቃተ ሕሊና የደፈጠጠ ሰብዓዊ ክብራቸውን ያጎደፈ በመሆኑ የተለየ አድርጎታል። በዚህም የተነሳ አገዛዙ ባልጠበቀውና ባላሰበው ሁኔታ ከሕዝቡ ኃይለኛ ተቃውሞ ስለገጠመውና ሥስ ብልቱ በመነካቱ ያለምንም ርህራሄ ዓይን ያወጣ የግፍና የጭካኔ እርምጃ በሕዝቡ ላይ ወስዷል፤ አሁንም እየወሰደ ይገኛል። በዚህ ሰብዓዊነት በጎደለውና በምንም ዓይነት ሊደገፍ በማይችለው ተቃዋሚዎቹን ለመደምሰስ እየወሰደ ባለው እርምጃ ቁጥራቸው ለጊዜው በግልጽ ያልታወቀ በርካታ ኢራናውያን በሞራል ጠባቂና በደህንነት ፖሊሶች ሕይወታቸው ጠፍቷል። በርካታዎችም ቆስለዋል። ለቆሰሉት ደግሞ የሕክምና እርዳታ ማግኘት አለማግኘታቸው ምንም የታወቀ ነገር አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የቅርብ ዘመዶቻቸውም እሳካሁን ድረስ ያሉበትን ለማወቅ አልተቻላቸውም። ብዙዎች ደብዛቸው ጠፍቷል። ለእስር ተዳርገዋል።

የዚህ ሕዝባዊ አመጽ ልዩ ምልክት ሆኖ ሊወጣ የቻለው ተካፋዮች በብዛት ሴቶችና ወጣቱ ትውልድ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በግንባር ቀደምትነት ሕዝባዊ አመጹንም እየመሩ መገኘታቸው ነው። የሀገራቸውንም ሆነ የራሳቸውን የወደፊት እድል በራሳቸው ለመምራት የሚያስችላቸውን መብት ለመጎናጸፍ፤ በግብረገብ ጠባቂ ፖሊሶች መንገላታታቸው እንዲቆም፤ የመናገር፥ የመጻፍ፥ ሃሳባቸውን በነጻ የመግለጽና ከማንኛውም የዜና ተቋም ያለምንም ገደብ ዜና የማግኘት መብታቸው እንዲከበር፣

ኑሯቸው እንዲሻሻል በከፍተኛ ደረጃ  እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። የኢራን ሕዝብ ጥያቄዎቹን በአደባባይና ሰላማዊ በሆነ መንገድ በማቅረቡ ከአገዛዙ የደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ፥ አፈናና ስቃይ የማንንም ሰብዓዊ ፍጡር መብት የሚጻረር በመሆኑ በጥብቅ የሚወገዝ ነው።

ሰላም ወዳድና ዴሞክራሲያዊ የሆነው የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በሙሉ ሊደግፉቸውና የትግል አንድነቱን ሊገልጽላቸው የሚገባ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ይህንንም እየገለጸ ይገኛል። ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል የተወለደው ኢሕአፓም የዚሁ ማህበረሰብ አባል በመሆኑ የትግል አንድነቱን ለኢራን ታጋዮች ይገልጻል። በተለይም የኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል እንቅስቃሴ ወቅት በአለም አቀፍ ደረጃ ይንቀሳቀሱ የነበሩ የኢራን ተማሪዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉትን የትግል አንድነትና አጋርነት ስናስታውስ የእንቅስቃሴያቸውን ምንነት ተገንዝቦ የትግል አንድነትን መግለጹ አግባብነት ያለው ነው የሚል የጸና እምነት አለን። የኢትዮጵያ ሕዝብም በግንቦት 2005 ዓ.ም. በተደረገው ምርጫ በመለስ አገዛዝ ላይ ድልን ቢጎናጸፍም፣ ይህን ሕዝባዊ ድሉን በጠመንጃ ኃይል መነጠቁን በመቃወም ባደረገው ተጋድሎ በርካታ ዜጎች የተገደሉበት፤ የታሰሩበት፤ ለእንግልት የተዳረጉበት፤ ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ደብዛቸው የጠፉበት ብሎም እነሆ እስከዛሬም ድረስ ከፍተኛ በደል እየደረሰበት ስላለ የኢራንን ሕዝብ መከራና ስቃይ በሚገባ የሚረዳለት ነው። ሀዘናቸው ሀዘኑ፡ ጭንቀታቸው ጭንቀቱ፡ ብሶታቸውም የሱም ነውና ዛሬ ከነሱ ጎን በመቆም የትግል አንድነቱን በማስተጋባት ትግላቸውን ከልብ እየደገፈ ድልም እንዲጎናጸፉ ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል። ከኢራን ህዝብ ቀጣይ ትግልም ተገቢውን ትምህርት የመቅሰሙ አስፈላጊነት ምንም ጥርጥር የለውም።

የተጨቆነው ብዙሃኑ የኢራን ሕዝብ ድሉን ይቀዳጃል!!
በዓለም አቀፍ ደረጃ፣ የሀገር ወዳዶች የትግል አንድነት ይጠንክር!!
በወያኔ አገዛዝ ላይ ማዕቀባችን ይጠንክር!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France